በዕውቀቱ ስዩም “የእሳት ዳር ሃሳቦች” በሚል ርዕስ ካሳተመው

<u>ዳዊትና ጎልያድ</u>

እግዜርና ዳዊት አብረው ተቧደኑ
ብቻውን ታጠቀ ጎልያድ ምስኪኑ
አንዳንዱ ለሽንፈት ተገዶ ሲፈጠር
በጥቅሻ ይወድቃል እንኳንስ በጠጠር

<u>ገበያ</u>

የሌሊት ወፍ ሲሆን ሽማቹ በሞላ
ጨለማህን ሽጠህ እንጀራህን ብላ

የሚቀጥለው ደግሞ ”ኗሪ አልባ ጎጆዎች” በሚል ርዕስ ካሳተመው

<u>ጣይና አንሺ ...</u>

ደሞዙን ቢጥል አንስተው ጠጡበት
ባርኔጣውን ቢጥል ወስደው ደመቁበት
ከዘራውን ቢጥል ተመረኮዙበት
በሄደበት ሁሉ እየተከተሉ
በጣለው ሲያጌጡ በጣለው ሲያተርፉ
እራሱን ሲጥል ግን አይተውት አለፉ ::

በዕውቀቱ ስዩም ”እንቅልፍና እድሜ” በሚል ርዕስ አዲስ መፅሃፍ አሳትሟል።